# ኢትዮጵያ፦ 'ልዩ  ፖሊስ' አስር ሰዎችን ገደለ

***በልዩ ሃይሉ የተፈፀመው የመብቶች ጥሰት ይጣራ፤ ዝግ ወደሆነው የሶማሌ ክልል መግባት ይፈቀድ***

(ናይሮቢ። ግንቦት 17፣ 2004 ዓ.ም)- በኢትዮጵያ መንግሥት የሚደገፍ ታጣቂ ቡድን በወርኃ መጋቢት 2004 ዓ.ም በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባካሄደው ዘመቻ 10 ሰዎችን መረሸኑን ዛሬ የወጣው የሂዩማን ራይትስ ዎች መግለጫ ይፋ አደረገ። "ልዩ ፖሊስ" ተብሎ በሚጠራው ኃይል የተፈጸመ የአስር ሰዎች ጭፍጨፋን ጨምሮ ሌሎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በዝርዝር ሊታወቅ የቻለው የሂዩማን ራይትስ ዎች መርማሪ ቡድን በወርኃ ሚያዝያ በጎረቤት ሶማሊላንድ ተሰማርቶ በነበረበት ወቅት ነው።

በመጋቢት 7 ቀን በሶማሌ ክልል በገሻሞ ወረዳ ልዩ ስሟ ራቅዳ ተብላ በምትጠራ መንደር አንድ ነዋሪን ከታጣቂ ኃይሎች ጥቃት ለመታደግ የሞከረ ግለሰብ በልዩ ፖሊስ ኃይል አባል በተተኮሰበት ጥይት ተገድሏል። የራቅዳ መንደር ነዋሪዎች በተጠቀሰው ዕለት በወሰዱት የመልሶ ማጥቃት እርምጃም ሰባት የልዩ ፖሊስ አባላት የተገደሉ ሲኾን 12 ያህል ፖሊሶችም በዕለቱ እና በበነጋው አራት መንደሮች ላይ አሰሳ አድርገዋል። በአሰሳቸውም ወቅት ተሸሽገው የነበሩ ከ10 የማያንሱ ነዋሪዎችን ረሽነዋል። በተኩስ ልውውጥ መካከልም እንዲሁ ዘጠኝ ገድለዋል፤ ሌሎች 24 ሰዎችን ደግሞ አፍነው ወስደዋል። በተጨማሪም በርካታ ሱቆችን እና መኖሪያ ቤቶችን ዘርፈዋል።

የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር ሌዝሊ ሌፍኮው "የልዩ ፖሊስ ኃይል አባላቱ መገደል የፖሊሶቹን ጭካኔ የተሞላበት የመልሶ ማጥቃት ድርጊት ተገቢነት አያረጋግጥም። ይልቁንም ሕገ ወጥ የሆነው የልዩ ፖሊስ ኃይል በሱማሌ ክልል የሚያደርሰውን ሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲያቆም የኢትዮጵያ መንግስት አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስድ የሚያስገድድ ነው" ይላሉ። ሂዩማን ራይትስ ዎችም ለግድያው እና ለሰብዓዊ መብት ጥሰቱ ተጠያቂ በኾኑት ኃይሎች ላይ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስድ እንዲሁም ቀጣይ ጥፋቶች እንዳይከሰቱ አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲያስተላልፍ የኢትዮጵያ መንግስትን ይጠይቃል።

በኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር ሸማቂዎች እና በመንግሥት ጦር መካከል ያለው ውጥረት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ወቅት ነበር የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት "ልዩ ፖሊስ" የተባለውን ታጣቂ ኃይል በ1999 ዓ.ም በሱማሌ ክልል ያቋቋሙት። በተከታዩ ዓመትም ልዩ ኃይሉ በአሁኑ ጊዜ የክልሉ ፕሬዝዳንት እና በወቅቱ ደግሞ የክልሉ የደህንነት ዋና አዛዥ በነበሩት አብዲ ሞሐመድ (በልዩ ስም አብዲ ኢሌ) እየተመራ የኃይል እርምጃ መውሰድ ጀመረ።

በወታደራዊ ዘመቻ ሰበብ በሲቪል ዜጎች ላይ እየተፈጸሙ ላሉት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሁሉ ልዩ ፖሊስ ዋነኛ ሚና እንደሚጫወት ሂዩማን ራይትስ ዎች ይገልጻል። የልዩ ፖሊስ ሕጋዊ አካልነት ግልጽ አይደለም። ይሁንና እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች ታማኝ ምንጮች ከኾነ በክልሉ መሥተዳድር አማካይነት የኃይሉ አባላት ከማዕከላዊ መንግስት የስልጠና፣ የጦር መሣሪያ፣ የመለያ አልባሳት አቅርቦት እና ደመወዝ ይሰጣቸዋል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች ወደ ጎረቤት ሶማሊላንድ የተሰደዱ እና በአራቱ መንደሮች በመጋቢት ወር ስለተከሰተው ኹኔታ በጥልቅ ያስረዱ 30 ያህል ተጠቂዎችን፣ ዘመዶቻቸውን እንዲሁም ሌሎች የዓይን እማኞችን አነጋግሯል።

እንደ እማኞች ገለጻ ከሆነ ሰባቱ የልዩ ፖሊስ አባላት በመጋቢት ሰባቱ ግጭት መገደላቸውን ተከትሎ የራቅዳ መንደር ነዋሪዎች ምሽቱን በፖሊስ ተከበው አድረዋል። በበነጋው ማለዳም 23 ሰዎችን በመኪና ጭነው አጎራባች ወደኾነችው ጋልካ መንደር ጉዞ መጀመራቸውን እማኞች ይገልጻሉ። በጉዞ ላይም መኪናውን አስቁመው አምስት ሰዎችን መርጠው እንዲወርዱ በማዘዝ መንገድ ላይ ገድለው ጥለዋቸዋል። “አምስቱን ሰዎች የገደሏቸው ሦስት ፖሊሶች ሲሆኑ ግንባራቸውን እና ትከሻቸውን በሦስት በሦስት ጥይት መትተው ጥለዋቸዋል” ሲሉ አንድ ታስረው የነበሩ እማኝ ለሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጸዋል።

በመጋቢት ስምንት ማለዳ 12 ሰዓት ግድም የልዩ ፖሊስ ኃይል በሁለት ተሽከርካሪዎች በመሆን አዳድ በምትባለው መንደር ላይ ጥቃት ፈጽመዋል። ከማለዳው ጥቃት የተረፉ እና የጥቃቱ ሰለባ የቅርብ ወዳጆች እንደገለጹት የልዩ ፖሊስ አባላት በየቤቱ እየገቡ የጦር መሣሪያ ፈትሸዋል እንዲሁም ነዋሪዎችን እየጎተቱ ከቤታቸው አስወጥተዋል። ወደ ሰማይም ይተኩሱ ነበር። የጦር መሣሪያ የያዙ ነዋሪዎችም በአጸፋው ተኩስ ከፍተው ግጭቱ በመባባሱ ቢያንስ አራት ያህል ነዋሪዎች ተገድለዋል። በርካታ ነዋሪዎችም አካባቢውን ለቀው ተሰደዋል።

የመንደሪቱ ነዋሪዎች በጥቃቱ የተገደሉትን ለመቅበር በሚሞክሩበት ወቅት አካባቢውን ለቆ ሄዶ የነበረው ልዩ ፖሊስ ተመልሶ መንደሯን ወሯታል። ከቀትር በኋላ በድጋሚ በተከሰተው ግጭትም አምስት ሰዎች ተገድለዋል። በተጨማሪም አራት ሰዎችን ከቤታቸው በማስወጣት ገድለዋቸዋል። ወንድሟ የከብት ሐኪም እንደነበር የገለጸች እማኝ “ወንድሜን ከቤት ጎትተው አሰወጡት፤ ግንባሩን በጥይት መቱት በኋላም ጉሮሮውን ሰየፉት” ስትል ለሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጻለች።

እንደነዋሪዎች ገለጻ ከኾነ የልዩ ፖሊስ ኃይሉ በሌላኛዋ የወረዳው ቀበሌ ላንጌታ ለአምስት ቀናት ያህል በመቆየት የነዋሪዎችን እንቅስቃሴ ገድቧል፤ የእለት ተእለት ኑሯቸውንም አስተጓጉሏል። ከሁለት በማያንሱ መንደሮችም ሱቆችን እና መኖሪያ ቤቶችን ዘርፏል።

የመንግሥት ባለስልጣናት ከግጭቱ ጋር በተያያዘ ሦስት የልዩ ፖሊስ አባላትን በቁጥጥር ሥር እንዳዋሉ የሚገልጽ ነገር ግን በሦስተኛ ወገን ያልተረጋገጠ መረጃ ሂዩማን ራይትስ ዎች ደርሶታል። ይሁንና የተያዙት አባላት ክስ ተመስርቶባቸው ወይም በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ምርመራ እየተደረገ ይኹን የሚታወቅ ነገር የለም።

በተደጋጋሚ እንደሚስተዋለው በሱማሌ ክልል የሚካሄደውን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለሚያጋልጡ ሪፖርቶች የኢትዮጵያ መንግሥት ምላሽ የጋዜጠኞችን፣ የለጋሽ ተቋማትን፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን እንዲሁም የገለልተኛ አካላትን እንቅስቃሴ የሚገታ ኾኗል። በመኾኑም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ እና ክልላዊ መንግሥት ጉዳዩን ለሚያጣሩ ከነጻው የመገናኛ ብዙሃን እና ከሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ለተውጣጡ አካላት እንዲሁም ሕገወጥ ድርጊቶችን እና ግድያዎችን ለሚያጣራው የተባባሩት መንግሥታት ልዩ መልዕክተኛ ኹኔታዎችን ማመቻቸት አለበት ሲል ሂዩማን ራይትስ ዎች ያሳስባል።

“የኢትዮጵያ መንግሥት በሱማሌ ክልል ላይ በሠሩት ዘገባ ምክንያት ጋዜጠኞችን ለዓመታት ሲያስር እና ከአገር ሲያባርር ከርሟል። በመኾኑም ለጋሽ አገራት የመብት ጥሰቶች ተሸሽገው እንዳይቀሩ በማሰብ የኢትዮጵያ መንግስት ለጋዜጠኞች እና ለሰብዓዊ መብት ቡድኖች በሩን እንዲከፍት ጥሪ ማቅረብ አለባቸው” ሲሉ ሌኮፍ አጽንኦት ይሰጣሉ።

በመጋቢት ወር ላይ ስለተፈጸሙ ድርጊቶች ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት የሚከተሉትን ያንብቡ።

**በመጋቢት 2004 ዓ.ም በልዩ ፖሊስ ኃይል የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ *ያለፍርድ የተፈጸሙ ርሸናዎች እና ሌሎች ግድያዎች***

የዓይን እማኞች እና የተጎጂ ቅርብ ሰዎች ከሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ እንደገለጹት በመጋቢት ሰባት እና ስምንት የልዩ ፖሊስ ኃይል በፈጸመው ርሸና ከአስር የማያንሱ ሰዎች ተገድለዋል። ትክክለኛው የሟቾቹ ቁጥር ከዚህም ሊልቅ ይችላል።

በመጋቢት ሰባት ቀን የልዩ ፖሊስ ኃይል አባል አንድን የራቅዳ መንደር ነዋሪ ሲደበድብ ተመልክቶ ከጥቃት ለማስጣል የሞከረ አብዲቃኒ አብዱላሂ የተባለ ግለሰብ በተተኮሰበት ጥይት ሕይወቱ ወዲያውኑ ልታልፍ ችላለች። የመንደሩ ነዋሪ የኾኑ እማኞች እንደተናገሩት የፖሊሱ አባል አብዲቃኒን “ምን ልታደርግ ነው?” የሚል ጥያቄ ብቻ ከጠየቀው በኋላ ወዲያኑ ተኩሶ ገድሎታል።

ግድያውን ተከትሎም በልዩ ፖሊስ ኃይሎች እና በአካባቢው ነዋሪዎች መካከል ከፍተኛ የተኩስ ልውውጥ ተደርጓል። በራቅዳ መንደር በተካሄደው የተኩስ ልውውጥ ተሳትፈው የነበሩት ዘጠኝ ያህል የልዩ ፖሊስ አባላት ወዲያውኑ አካባቢውን ለቀው በአቅራቢያ ወደምትገኘው አዳዳ መንደር አምርተዋል። የመንደሩ ነዋሪዎች እና የአብዲቃኒ ቤተሰቦች የልዩ ሃይል አባላቱን በማሳደድ ተኩስ ከፍተው ሰባት ያህል የልዩ ፖሊስ አባላት ሊገደሉ ችለዋል።

በነጋታው ከረፋዱ አምስት ሰዓት ላይ 23 የራቅዳ ነዋሪዎችን በመኪና ጭነው ወደ ጋልካ መንደር ጉዞ መጀመራቸውን ታግተው ከነበሩት የራቅዳ ነዋሪዎች መካከል አንዱ ይናገራል። በጉዞ ላይ እንዳሉም ከታጋቾቹ መካከል አምስት ሰዎችን በመምረጥ ከመኪናው እንዲወርዱ አስገድደዋቸዋል። በመጨረሻም በጎዳናው ጠርዝ ላይ እንዲቀመጡ በማስገደድ ተኩሰው ገድለዋቸዋል። ሌላ እማኝም የእለቱን ኹኔታ እንዲህ ሲል ይገልጻል፤

> ከረፋዱ አምስት ሰዓት ግድም ከራቅዳ ወደ ጋልካ እየወሰዱን እያሉ ድንገት መንገድ ላይ የተጫንበትን መኪና አስቆሙት። የጭነት መኪናው በሌሎች አራት የልዩ ፖሊስ ተሽከርካሪዎች ታጅቦ ነበር። ከመካከላችን አምስት ታጋቾችን በመምረጥ እንዲወርዱ አስገደዷቸው። ከመኪናው አጠገብ ቆሞ የነበረ የልዩ ፖሊስ ኃይል “ግደሏቸው፤ ጨርሷቸው” የሚል ትዕዛዝ በማስተላለፉ በተጠንቀቅ ቆመው የነበሩት ሦስት ታጣቂዎች በነፍስ ወከፍ ሦስት ሦስት ጥይቶችን በመተኮስ አምስቱንም ታጋቾች ገደሏቸው። ሟቾቹ ግንባራቸውን እና ትከሻቸውን በጥይት ተደብድበው ነው የተገደሉት።

በሕይወት የተረፈ ሌላ ታጋች ደግሞ አምስቱ ሰዎች ጭንቅላታቸው ላይ በጥይት ተመትተው ሲገደሉ ተመልክቷል። እንደሱ ገለጻ ከኾነ ፖሊሶቹ "እንደእነሱ እንገላችኋለን" እያሉ ቀሪዎቹን ታጋቾች ያስፈራሩ ነበር።

በተመሳሳይ ቀን ማለዳ በአዳዳ መንደር ቤት ለቤት ሲያስሱ የነበሩት ልዩ ፖሊሶች አራት ሰዎችን እንዲሁ ረሽነዋል። ሂዩማን ራይትስ ዎች ከበርካታ የአይን እማኞች ተመሳሳይ መረጃ ደርሶታል። እንደመረጃውም ከመኖሪያ ቤታቸው በግዳጅ እንዲወጡ የተደረጉ ተጠቂዎች የጦር መሣሪያ ያልያዙ ሰላማዊ እና ሕይወታቸውን ለመታደግ ተሸሽገው የነበሩ ዜጎች ናቸው። ሁሉም ሟቾች ጭንቅላታቸውን ወይም አንገታቸን የተመቱ ናቸው።

ሰብዓዊነት በጎደለው አኳኋን ከተረሸኑት መካከል አንድ የከብት ሐኪም እንደሚገኝም የዓይን እማኞች ገልጸዋል። ፖሊሶቹ ሐኪሙን ከቤቱ እየጎተቱ ካስወጡት በኋላ በጥይት ግንባሩን መትተውታል። ይኹንና ግንባሩን ተመትቶ አለመሞቱን ሲያውቁ ጉሮሮውን ሰይፈውታል። ይህን አሰቃቂ ድርጊት የተመለከተችው በመካካለኛ ዕድሜ የምትገኝ የሟቹ ሐኪም እህት የሚከተለውን ምስክርነት ለሂዩማን ራይትስ ዎች ሰጥታለች፤

> ሰባት ያህል የልዩ ፖሊስ አባላት በቀጥታ ወደ ቤት ገብተው የቤቱ ባለቤት የት እንደሚገኝ ጠየቁ። ወንድሜን ከያዙት በኋላ እየጎተቱ አስወጡት። ግንባሩም ላይ በጥይት መትተው አንገቱን ሰየፉት። የወንድሜን ነፍስ ካጠፉ በኋላ ጠመንጃ የተቀመጠበትን ቦታ እንድትጠቁም ልጁን ጠየቋት። ነገር ግን ቁልፉን ማግኘት ባለመቻሏ የተበሳጩት ፖሊሶች ትከሻዋ ላይ በሰደፍ መተዋታል።

በተመሳሳይ ሂዩማን ራይትስ ዎች ከዓይን እማኞች እንዳገኘው መረጃ አንድን ዕድሜው በአስራዎቹ ውስጥ የሆነ ወጣት ከአጎቱ መኖርያ ቤት እየተጎተቱ በአቅራቢያ ከሚገኝ ሥፍራ ወስደው በጥያቄ አጣድፈውት ሲያበቁ በጥይት መትተውታል። አንድ ምስክርም እንደገለጸው ልጁ ከመገደሉ አስቀድሞ ጸሎት ሲያደርግ ሰምቷል፤ አስከሬኑም ቆሻሻ ከሚጣልበት ቦታ አጠገብ መሬት ላይ ተጥሏል። ሦስተኛው ሰለባ ደግሞ በእድሜ ጠና ያሉ ናቸው። ከቤታቸው በግዳጅ ከተወሰዱ እና ለአጭር ጊዜ በፖሊሶቹ ጥያቄ ከተደረገላቸው በኋላ በቆሙበት በጥይት ተመትተዋል። ቁጥራቸው በርከት ያለ የአይን እማኞች ሟቹ ፖሊሶቹ እንዳይገሏቸው ሲማጸኑ መስማታቸውን ተናግረዋል። አራተኛውም ተጠቂ እንዲሁ ከቤቱ በግዳጅ እንዲወጣ በተደረገበት ቅጽበት ውስጥ ተገድሏል።

ቢያንስ ዘጠኝ ሌሎች የአዳዳ ነዋሪ ግለሰቦች በልዩ ፖሊስ አባላት እንደተገደሉ መረጃዎች ያሳያሉ። ይሁንና ስለአሟሟታቸው ግልጽ የኾነ መረጃ የለም። አንዳንድ መረጃዎች ግን በልዩ ፖሊስ ኃይሎች እና በመንደሩ ታጣቂ ነዋሪዎች መካካል በተደረገ የተኩስ ልውውጥ ሳይሞቱ እንዳልቀሩ ያሳያሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የዓይን እማኞች እንደሚናገሩት ለመሸሽ በሞከሩ ነዋሪዎች ላይ ፖሊሶች ተኩስ ከፍተው ብዙዎቹን ጭንቅላታቸው ላይ እና ከወገባቸው በላይ በመምታት ገድለዋቸዋል። ሁለት ሰዎችም በልዩ ፖሊስ ተሽከርካሪዎች ተጨፍልቀው ለሕልፈት ተዳርገዋል።

*አፍኖ መውሰድ፣ ማሰቃየት እና ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ*

የልዩ ፖሊስ ኃይል አባላት በአዳዳ መንደር ዘመቻ ባደረጉበት ወቅት ቢያንስ ሦስት ሴቶችን ጨምሮ በርካታ ነዋሪዎችን አግተው ወስደዋል፣ ገርፈዋል እንዲሁም ሰብዓዊነት በጎደለው ኹኔታ አንገላተዋል።

በመጋቢት ስምንት ቀን በልዩ ፖሊሶች አስገዳጅነት ከቤቱ እንደተወሰደ የሚናገር የአዳዳ ነዋሪ ስለኢ-ሰብዓዊ አያያዛቸው የሚከተለውን እማኝነት ለሂዩማን ራይትስ ዎች ተናግሯል፤

> አራት ፖሊሶች ከቤቴ እንደደረሱ ባለቤቴን ትንፍሽ እንዳትል አስጠነቀቋት። በተመሳሳይ አራት ሰዎች ከደጃፍ ቆመው ይጠብቁን ነበር። ከዛም ከቤቴ አንጠልጥለው አስወጡኝ፤ መሣሪያዬንም በርብረው ወሰዱ። በሰደፍ እያላጉም በቅርብ ርቀት ወደሚገኘው አነስተኛ ኸረት ወሰዱኝ። ከሥፍራው እንደደረስንም አንገቴን በቀበቶ ሲያንቁኝ ራሴን ሳትኩ። 15 ሜትር ጥልቀት ወዳለው 'በርከት' (ኩሬ) ወርውረው ሲያበቁ በዛፍ ቅርንጫፍ ሸፈኑኝ። ኩሬው ጭቃ ስለነበረው እንደነቃሁ ለመውጣት ችያለሁ።

በአዳዳው ዘመቻ ወቅት ቁጥራቸው ከሦስት የማያንስ ሴቶች በልዩ ፖሊስ ተደብድበዋል። ባለቤቷ በቤት ውስጥ እንዳልተሸሸገ በመናገሯ በፖሊሶች ድብደባ እንደደረሰባት አንዲት ወጣትም ተናገራለች። "አንቺ ዋሽተሽናል አሉኝ። ከዛም ደበደቡኝ በሰደፍም ፈነከቱኝ። በድብደባው የተነሳ ኩላሊቴ ላይ ቁስለት ነበረብኝ። ጥርሴንም አጥቻለሁ።"

መጋቢት ስምንት ቀን ታፍነው እንደተወሰዱ ለሂዩማን ራይትስ ዎች የገለጹ ሦስት የራቅዳ ነዋሪዎች ደግሞ እያንዳንዳቸው ለዘጠኝ ቀናት ታስረዋል። በመጀመሪያዎቹ 24 የእስር ሰዓታት የሚጠጡት ዉሃ አላገኙም ነበር። ከአካባቢው ነዋሪዎች ምናልባትም ደግሞ ከፌዴራሉ ባለስልጣናት ለመሸሸግ በሚመስል ኹኔታ ለተከታታይ አራት ቀናት በየመንደሩ እና በአነስተኛ ከተሞች በመኪና ሲያሽከረክሯቸው እንደነበር የአይን እማኞቹ ይናገራሉ።

በመጀመሪያዎቹ አራት የእገታ ቀናትም ፖሊሶች ታሳሪዎችን በዱላ እና በሰደፍ ደብድበዋል። ከሁለት በማያንሱ አጋጣሚዎች እንዲሁ ታሳሪዎቹን በመክበብ የመረሸን ሙከራ በማድረግ አስፈራርተዋቸዋል። ይኹንና በልዩ ፖሊስ አባላት መካከል ልዩነት በመፈጠሩ ምክንያት የታጋቾቹ ሕይወት ሊተርፍ ችሏል። ለሂዩማን ራይትስ ዎች ምስክርነቱን የሰጠ ከታጋቾቹ አንዱ እንዲህ ይላል፤

> በመኪና ጭነው በተለያዩ መንደሮች በሚያሽከረክሩን ወቅት አንዳንድ ፖሊሶች የፌደራል መንግሥት ችግር እንዳይፈጥርባቸው በሚመስል ሁኔታ እኛ እንድንፈታ ይሟገቱ ነበር። ወንጀል የሰራን ይመስል የስነስርዓት ርምጃ ይወስዱብናል። ሌሎቹ ደግሞ "24ቱንም እንግደላቸው" ሲሉ ተደምጠዋል። በፖሊሶቹ መካከል የተለያየ ኃሳብ ይንጸባረቅ ነበር።

ከአራቱ ቀናት የመኪና ውስጥ እገታ በኋላም ቢኾን እስራቱ አልቀረላቸውም። ላንጌታ ወደተባለችው መንደር አቅራቢያ ተወስደው ለአራት ቀናት ያህል በጠራራ ጸሐይ ሜዳ ላይ ታግተው ከርመዋል። መጠነኛ ምግብና ዉሃም ያገኙ ነበር። ወደ

ገሻሞ መንደር ከተወሰዱ በኋላም በክልሉ መንግሥት እና በጎሳ መሪዎች መካካል በተደረገው ድርድር ምክንያት መጋቢት 16 ቀን ታሳሪዎቹ ነጻ ወጥተዋል።

**ዝርፊያ**

የልዩ ፖሊስ አባላት የተለያዩ ቁሳቁሶችን፣ ምግብ እና ገንዘብ ከሱቆች እና ከግለሰቦች መኖሪያ ቤት መዝረፋቸውን የአዳዳ እና ላንጌታ ነዋሪዎች ይናገራሉ። ሂዩማን ራይትስ ዎች ያናገራቸው ስድስት ነዋሪዎች እንደገለጹት የቤት ቁሳቅስ፣ ጌጣጌጥ እንዲሁም ሌሎች ንብረቶች በመጋቢት ስምንት ቀን ተዘርፈውባቸዋል።

በላንጌታ መንደር የሚኖሩ የ45 ዓመት ባልቴት እንደተናገሩት ከአምስት እስከ ሰባት የሚገመት የአባላት ብዛት ያሉት የፖሊስ ቡድን በመንደሯ ከሚገኙ 10 መደብሮች ውስጥ ሲገባ ተመልክተዋል። ሁለት ወይም ሦስት ፖሊሶች ሱቅ ውስጥ በመግባት ጫማ፣ አልባሳት፣ መጠጦች እና ምግብ ሰርቀዋል። ሁለት ወይዛዝርትም እንደተናገሩት መላ ንብረታቸውን በመዘረፋቸው ምክንያት ወደመንደራቸው ለመመለስ አልቻሉም።

በጎረቤት ሶማሊላንድ የሚገኙ የአካባቢ ባለሥልጣናት እንደጠቆሙት ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ከተጎጂ መንደሮች በተውጣጡ የጎሳ መሪዎች እና በክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት መካከል ውይይት ተካሂዷል። ይሁንና ሂዩማን ራይትስ ዎች ያነጋገራቸው የአካባቢው ነዋሪዎች በአጠቃላይ ወደ መንደራቸው ለመመለስ የቅርብ ጊዜ ዕቅድ የላቸውም።

**ተጨማሪ መረጃ**

የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ለኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) የትግል ሥፍራ በመኾን ከአሥር አመታት በላይ ዘልቋል። በአብዛኛው በኦጋዴን ጎሳ አባላት የሚደገፈው እና የሱማሌ ሕዝብን ያማከለ ትጥቅ ትግል የሚያደርገው ኦብነግ ለክልሉ ሰፋ ያለ ፖለቲካዊ የራስ ገዝ አስተዳደርን የሚሻ ነው። በሚያዝያ 1999 ዓ.ም ለ70 ንጹሃን ዜጎች ሞት እና ለበርካታ የቻይና ነዳጅ ባለሞያዎች መታገት ምክንያት የኾነውን የኦብነግ የአቦሌ የነዳጅ ሥፍራ ጥቃት ተከትሎ የኢትዮጵያ መንግሥት ቀድሞውኑ በጦርነቱ በተጎዱ አምስት የክልሉ ዞኖች ላይ የጥቃት ዘመቻ ከፍቷል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች እ.ኤ.አ በሰኔ 2008 ዓ.ም በግጭቱ ምክንያት ስለተከሰቱት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ባቀረበበት የምርመራ ዘገባ እንዳስቀመጠው ከ1999 ኢጋማሽ እስከ 2000 ባሉት ጊዜያት ባካሄዱት ግጭትወቅት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊት እና ኦብነግ የጦር ወንጀሎችን ፈጽመዋል። በዚህም የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ግድያ፣ማሰቃየት፣ አስገድዶ መድፈርን እንዲሁም በኃይል ማፈናቀልን የመሳሰሉት ወንጀሎች የተፈጸሙበትን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት በሰብአዊ ፍጡር ላይ በተፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

እነዚህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በገለልተኛ ወገን አልተጣሩም። እ.ኤ.አ በሂዩማን ራይትስ ዎች ለወጣው ዘገባ መልስ ለመስጠት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በ2008 ዓ.ም ማጣራት አድርጎነበር። ይኹንና ተደረገ የተባለው ማጣራት አንድ ተአማኒ ምርመራ የሚፈልጋቸውን መሠረታዊ የገለልተኛነት፣ ወቅታዊነት እንዲሁም ምስጢራዊነት መስፈርቶች ያሟላ

አልነበረም። በክልሉ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በነፃ አካላት እንዲጣሩ ለሚቀርቡ ተደጋጋሚ ጥሪዎች መንግስት ምላሽ ሳይሰጥ ቆይቷል።

ከ1999ኙ የተፋፋመ ግጭት ወዲህ በሱማሌ ክልል ያለው የነፃ ጋዜጠኞች እና የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪዎች እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ ቁጥጥር ሥር ወድቋል። በሐምሌ 2003 ዓ.ም በክልሉ ያለውን ግጭት ለመዘገብ ወደ ክልሉ የገቡ ሁለት የስዊዲን ጋዜጠኞች ተይዘው ግልጽነት በጎደለው እና ለብዙ ትርጉሞች ክፍት በኾነው የጸረ-ሽብር ሕግ የ11 ዓመት እሥራት ተፈርዶባቸዋል።

በወርሃ መጋቢት ግጭት የተካሄደበት ገሻሞ መንደር የሚገኘው በጦርነት ከተጎዱት አምስት ዞኖች መካከል አንዱ በሆነው ደገሃቡር ነው።፡ይሁንና ባለፉት ዓመታት በነበረው ግጭት ቀጥታ ተጎጂ አልነበረም። ለኦብነግ እንደ ድጋፍ ምንጭነት የማይታዩት የኢሳቅ ጎሣ ሶማሌዎች በብዛት የሚኖሩበት ዞን ነው።